የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፸፭
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፯ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No 75
ADDIS ABABA, 3th August 2017.

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፵፬/፪ሺ፱ ዓ.ም
ለአይሻ የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከቻይና ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ገፅ ……….፱ሺ፰፻፲፰

CONTENT

Proclamation no.1044/2017
Export-Import Bank of China loan agreement for financing the Aysha Wind Power Project Ratification Proclamation page …………….9818

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፵፬/፪ሺ፱

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለአይሻ የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ፪፻፲፰ ሚሊዮን ፮፻፺፪ ሺ ፬፻ የአሜሪካ ዶላር / ሁለት መቶ አስራ ስምንት ሚሊዮን ስድስት መቶ ዘጠና ሁለት ሺ አራት መቶ የአሜሪካ ዶላር / የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግስት እና በቻይና ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል ግንቦት ፬ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በቤጂንግ የተፈረመ ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፤-

## PROCLAMATION No.1044/2017

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENET BETWEEN THE GOVEREMENT OF FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND EXPORT-IMPORT BANK OF CHINA

**WHEREAS ,** a loan agreement between the Government of Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export-Import Bank of China stipulating that the Export-Import bank of China provide to the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan in an amount equivalent to 218,692,400.00 USD (two hundred eighteen million, six hundred ninety two thousand, four hundred United States Dollar) for financing the Aysha Wind Power Project was signed in Beijing on the 12th day of May 2017;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Loan Agreement at its session held on 5th day of July 2017;

**Now, therefore,** in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

www.chilot.me

፩. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ “ለአይሻ የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከቻይና ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል የተገኘን የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፵፬/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **<u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል ግንቦት ፬ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በቤጂንግ የተፈረመውን ቁጥር China Exim bank PBC. No (2017) 8 TOTAL No.(434) የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፅድቋል ፡፡

፫. **<u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፪፻፲፰ ሚሊዮን ፮፻፺፪ ሺ ፬፻ የአሜሪካ ዶላር /ሁለት መቶ አስራ ስምንት ሚሊዮን ስድስት መቶ ዘጠና ሁለት ሺ አራት መቶ የአሜሪካ ዶላር / በብድር ስምምነቱ በተመለከቱ ሁኔታዎች መሰረት በስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

፬. **<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፯ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ፕሬዚዳንት**

1. **<u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the “Export-Import Bank of China Loan Agreement for financing the Aysha Wind Power Project Ratification Proclamation No.1044/2017”.

2. **<u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement China Exim Bank PBC. No (2017) 8 TOTAL No. (434) signed on 12th day of May 2017 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export-Import Bank of China is hereby ratified.

3. **<u>Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation</u>**

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount to 218,692,400.00 USD (two hundred eighteen million, six hundred ninety two thousand, four hundred united states dollar) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. **<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force upon publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 3th day of August 2017.**

**MULATU TESHOME (DR.)**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

www.chilot.me

www.chilot.me

www.chilot.me